# 2. ሐኪም መታየት

## ጠቅላላ የቤተሰብ ሐኪም

- በአውስትራልያ ውስጥ ብዙ ሰዎች ሲታመሙ ወይም ለመመርመር ሲፈልጉ ወደ የቤተሰብ ጠቅላላ ሐኪም ይሄዳሉ። አንዳንድ ጊዜ የቤተሰብ ሐኪሞች 'ጠቅላላ ሐኪሞች' ('general practitioners') (GP) ተብሎም ይጠራሉ።
- የቤተሰብ ሐኮሞች የእርስዎ ጠቅላላ የሆነ አካላዊ እና ስሜታዊ ጤና ይመረምራሉ፤ እና አጣዳፊ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ብዙ ሰዎች የጤና ችግር ካጋጠማቸው ወደ እነሱ ይሄዳሉ።
- ማንኛውም ዓይነት ምርመራ ካፈለገ፣ ስፔሻሊስት ጋ መሄድ ካስፈለገ፣ ወደ ሆስፒታል መሄድ ካስፈለገ፣ ወይም ደግሞ ያጋጠምውን የጤንነት ችግር ራሳቸው የሚያክሙት ከሆነ ውሳኔ የሚሰጡት የቤተሰብ ሐኪሞች ናቸው።
- የቤተሰብ ሐኪሞች 'የሕክምና ማእከላት' ('medical centres') ወይም 'ሰርጀሪስ' ('surgeries') ተብሎ በሚጠሩ ትናንሽ ማእከሎች ሆነው ያክማሉ። እነዚህ ማእከሎች፡ አብዛኞቹ ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጥዋቱ 9 እስከ 5 ከሰዓት ባለው ጊዘ ውስጥ ይከፍታሉ። ነገርግን አንዳንዶቹ ከዚህ ረዘም ላለ ጊዜ እና እንዲሁም ደግሞ ቅዳሜ እና እሁድ ይከፍታሉ። በጣም ጥቂቶች ደግሞ በቀን 24 ሰዓት ይከፍታሉ።
- የራስዎ የቤተሰብ ሐኪም ለመምረጥ ይችላሉ። ከቤተሰብ ሐኪሙ በሚያገኙት አገልግሎት ደስተኛ መሆን አስፈላጊ ነው። ካልሆነ ሌላ መምረጥ ይችላሉ።
- አስተርጓሚዎች ማቅረብ የሚችል ወይም የእርስዎ ቋንቋ መናገር የሚችል የቤተሰብ ሐኪም ለማግኘት እንዲችሉ፡ ጓደኞች፣ የቤተሰብ አባሎች፣ ወይም በአከባቢው የሚኖሩ ሰዎች መጠየቅ በጣም አስፈላጊ ነው። በሌላ አማራች ደግሞ፡ የለው ፔጅ በሚባለው የቴሌፎን ማውጫ ላይ 'medical practitioners' በሚለው አርእስት ስር ማየት ይችላሉ።

Interpreter

## ለሐኪሙ መክፈል

- አንዳንድ ሐኪሞች ደግሞ ለበሽተኞቻቸው የ'bulk bill' የሚባለውን አገልግሎት ይሰጣሉ። ይህ ማለት ደግሞ በቤተሰብ ጠቅላላ ሐኪም ለመመርመር አያስከፍልዎትም ምክንያቱ፡ የፌዴራል መንግስቱ በመዲኬር በኩል አድርጎ ለሐኪሙ በቀጥታ ስለሚከፍለው ነው።
- ሐኪምዎ የ'bulk bill' አገልግሎት ካልሰጥዎ፡ ለሐኪሙ ከከፈሉ በኃላ የከፈሉበት ደረሰኝ በማሳየት ገንዘቡን ከመዲኬር እንዲከፈልዎት ሊጠይቁ ይችላሉ። ይህ ማለት ደግሞ እርስዎ የሚከፍሉት በሁለቱ ክፍያ መካከል ያለውን ልዩነቱ ብቻ ነው።
- የመዲኬር ካርድ ካልዎት ብቻ ነው bulk billed ማድረግ የሚችሉ ወይም ደግሞ፡ ገንዘብ እንዲመለስልዎት ከመዲኬር መጠየቅ የሚችሉ። የመዲኬር ካርድ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉና፣ ለዚህም እንዴት ብቁ እንደሚሆኑ፣ እንዲሁም መቼ እና እንዴት መክፈል እንዳለብዎት ለማወቅ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ወደ 13 20 11 ይደውሉ ወይም በ http://www.medicareaustralia.gov.au/ ይመልከቱ።

## ቀጠሮ

- ጠሮ አስተድመው መያዝ አለብዎት
- ቀጠሮ ብዙ ጊዜ አጭር ጊዜ ይወስዳል (10- 15 ደቂቃዎች) ነገርግን ካስፈለገ ቀጠሮ በሚይዙበት ጊዜ ረዘም ያለ የቀጠሮ ጊዜ ለመጠየቅ ይችላሉ፡
- ያለቀጠሮ ከመጡ፡ እንዲሄዱ ወይም ለረጅም ጊዜ እንዲጠብቁ ሊጠየቁ ይችላሉ
- አንድ ቀጠሮ ለአንድ ሰው ብቻ ያገለግላል
- በቀጠሮ ጊዜ ላይ ለመገኘት የማይችሉ ከሆነ፡ ሐኪምዎ ጋ ደውለው መንገር አለብዎት
- ከሐኪሙ ጋ ስለምን መናገር እንደሚፈልጉ ጽፈው ከመጡ፡ በቀጠሮው ጊዜ ጥሩ ሊተቀሙ ይችላሉ
- በአሁን ጊዜ እየወሰዱት ያሉ መድሀኒቶች በሙሉ፡ ባህላዊ መድሀኒቶች፣ ቫይታሚኖች፣ ዕፆች ወዘተ ሐኪሙን ማሳወቅ ይኖርብዎታል
- 

ይህ መረጃ ጽሑፍ 10 ተከታታይ ክፍሎችን የያዘ ነው። በሙሉ ሲታይ፥


1፡ የጤና አጠባበቅ ዘዴ በኲንስላንድ
2፡ በሐኪም መታየት
3፡ መድሀኒቶች
4፡ የኲንስላንድ ሆስፒታሎች
5፡ የኮሚኒቲ የጤና ማእከላት
6፡ የጥርስ ሕክምና አገልግሎቶች
7፡ አላይድ (Allied) የጤና አገልግሎቶች
8፡ በጤንነት መኖር እና በሽታን መከላከል
9፡ ለተለዩ ብዱኖች የሚሰጥ የጤና እና የድጋፍ አገልግሎቶች
10፡ እርስዎ እና የጤና አገልግሎት ዘዴ ያካትታል።